ለወቃሻ ሰነፍ

ሰኔ 24: 2004:

ጀግንነት ያልገባዉ ጀግናነት የሚሻዉ
በዚህ ዓለም ጫካ መራመድ ያቃተዉ
ጫካዉ ዉስጥ ተቀምጦ ታሪክ ሊያዋካ
ሲዋልል የኖረዉ ሰነፉ ወክዋካ
ስያልም ያድራል ስዋዥቅ ይኖራል
ወደፊት እያለ ስያይ ወደኋላ
ያላገኘዉ እጦት በዉስጡ ስብላላ

ጀግንነት ጥሎት ያልፋል
ጀግና ጥሎት ያልፋል
ለታሪክ ታዞ በወኔ ተጠርቶ
ፈልጎት ሳይሄድ ተፈልጎ ተገኝቶ
ፍርሃት ሳይይዘዉ ከቶ ሳይቃጣዉ
ወደፊት ተራምዶ ራስን ኣጋፍጦ
ለነሱ ብሎ ያለውን ኣማጦ
ይወድቃል ይዋደቃል ታሪክን ኣጊጦ
ጀግንነት ይህ ነዉ ጊዜ የምያመጣው
ጀግናነት ይህ ነዉ ቅጽበት የምወልደው

ባሩድን ኣግኝቶ ወትፎ ወርዋሪዉን
ከደጃፉ ዘልቆ መቆጣጠር የቃጣዉን
ጊዜ ይወልደዋል ኦኔ የጠራዉን
ተነስቶ ያሳያል ደረቱን: ጋሻቸዉን
የኦኔዉ ቆራጥነት የጋሻቸዉን ብርቱነት
ያስመሰክረዋል የባሩዱን አፈርነት
ለዓለም ያሳያል የወርዋሪዉን ሽንፈት
በግልጽ ይፈነጥቃል የሰዉን እኩልነት

ያ ነበር የትላንቱ ቅጽበት
ያስቀመጠዉ ታሪክ በቆራጥ ወኔነት

ያለፈዉን ትተን ስንራመድ በእኩልነት
የትላንቱ ቅጽበት ያልወለደዉ ሰራዊት
ይንጋጋ ዛሬ ለትላንት ጦርነት?
እንዲህ ተዘናግቶ ለዛሬዉ ወራሪነት?

ኣዉቃለሁ ብሎ ይዞ ድንቁርና

ምድር ተናወጠች? ራሱን ሊያቀና?

ከምእራቡ ባሩድ ከምስራቅ ዓየር

የዛሬዉን ማዛባት የትላንቱን ኣፈር

ትላንት በኦኔነት ዛሬ በሊቅነት

ለዓለም ኣስምረን የሰዉን እኩልነት

ኣንደኛዉን አደዋ ለባሩድ ወርዋሪዉ

ሁለተኛዉን አደዋ ለማዛባት ቀዣባሪዉ

የትላንቱ ባንዳ የዛሬዉ ወራዳ

የዛሬዉም ባንዳ የነገ ወራዳ

ዓለች ምድራችን የጀግና መባቻ

ትኑር ቄያችን የታሪክ መሰንበቻ

የጫካዉን ምሬት ጣዕሙንም ኣጣጥማ

ለሁሉም ያሳየች የመኖርን ኣላማ

ሁሉን የታደገች ያለምንም ዓቻ

ሁሉን የምታድግ ዓቻ ለዓቻ

ለዓለም የፈነጠቀች የዓቻን መባቻ

ዓለምን የመራች ወደ ዓቻ መባቻ

ከቻለ ማስተዋል ጀግንነትን የምሻዉ

ስንፍናን ይዞ ሲዋልል የኖረዉ

የጀግና ምንነት የነገን ሰዉ ይበለው

መታሰብያነቱ

ለአርጊ አመኒ: ልብነ ድንግል

ሁለተኛዉ ምንሊክ: ጣይቱ ብጡል

ገራሱ ዱኪ: ሐብተግዮርጊስ ድነግዴ

ጃገማ ኬሎ: ጎባና ዳጬ

ባልቻ አባ ነፍሶ: አሉላ አባ ነጋ

ዘራይ ደረስ: አብዲሳ አጋ

ኣብረሃ ደቦጭ: ሞገስ አስገዶም

አበበ ኣረጋይ: ኣቡነ ጴጥሮስ

ሃይለ ስላሴ: ታደሰ ብሩ

በላይ ዘለቀ: ናዲ ገመዳ

ቡሪሶ ቦሩ: ብርቱካን ሚደክሳ

እና ሌሎች የሃገራችን ጀግኖች

የቋንቋ ትምህርት እና ችሎታ ያላችሁ ይህን ግጥም ያለምንም ፈቃድ ይዘቱን ሳይለውጡ ግጥሙን ለማሻሸል እና ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ለመተርጎም ተጋብዘዋል